## ቢሆንስ....

- የንብረት አስተዳደር ኩባንያ ልጆች ያላቸው የቤተሠቦች መከራየት የሚችሉት የመጀመሪያ ፎቅን ነው የሚል መመሪያ ቢወጣ?
- አከራዩ ከሰሜን ምዕራብ አካባቢ ይልቅ ምቹው የሰሜን ምሥራቅ አካባቢ ነው ብሎ ቢነግሮትስ?
- እንበል በጋዜጣ ላይ ስለሚከራይ ቤት አንብበው ስለክፍሉ ሲጠይቁ «ተከራይቷል» ቢባሉና ከጥቂት ቀናት በኋላ ቤቱ አሁንም እንዳልተከራየ በጋዜጣ ላይ ቢያነቡ ምን ይላሉ?
- አከራዩ የላቲን ዝርያ ያላቸው ተከራዮች የኪራይ ክፍያዎን በጥሬ ገንዘብ መክፈል አለባቸው የሚል መመሪያ ቢያወጣ ምን ይላሉ?

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት አባባሎች የቤት አገልግሎት እንዳያገኙ የሚያግዱ መድልዎች ሲሆኑ፤ በዲ.ሲ. የሰብአዊ መብቶች ሕግና በቤቶች አስተዳደር ሕግ ፈጽሞ የተከለከሉ ናቸው።

**በዚህ ረገድ መብቶ የተረገጠ ወይም የተጣሰ ሆኖ ከተሰማዎ በሚከተለው አድራሻ ለሰብአዊ መብቶች ጽ/ቤት ያመልክቱ። ስልክ (202) 727-4559 ወይም የድህረ መረብ አድራሻ፦ www.OHR.dc.gov**

ስለ እኩል መብት የተሰጠ መግለጫ

1. ስምዎትንና አድራሻዎትን
2. አቤቱታ የሚያቀርቡበትን ግለሠብ ስምና አድራሻ
3. ስለመብት ረገጣው የሚገልጽ አጭር ማብራሪያ
4. የመብት ረገጣው የተፈፀመበት ቀን

ስለ እኩል መብት የተሰጠ መግለጫ

እ.ኤ.አ. በ1977 በወጣው የዲ.ሲ የሰብአዊ መብቶች ሕግ እንዲሁም በተሻሻለው የዲ.ሲ. ይፋዊ ሕግ አንቀጽ 2-1401.01 መሠረት የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የዘር፣ የቀለም፣ የሐይማኖት፣ የብሔር፣ የፆታ፣ የዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የመልክ፣ የወሲብ ዝንባሌ፣ የቤተሰብ ደረጃ፣ የቤተሰብ ኃላፊነት፣ የትምህርት ደረጃ፣ የፖለቲካ፣ የአካል ጉዳተኝነት፣ የገቢ ወይም የመኖሪያ እና የንግድ ቦታ መድልዎ አያደርግም። በተጨማሪ ሕጉ የወሲብ ጥቃትን እንደያታ መድሎዎ በመቁጠር ድርጊቱን ይቃወማል፣ ይከለክላልም። ይህን ሕግ መጣስ ያስቀጣል። ግዛቱ ሕጉን በማያከብሩ ነዋሪዎች ላይ አስፈላጊውን የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ይወስዳል።

የሰብአዊ መብቶች ጽ/ቤት በአሜሪካ የቤቶች እና የከተማ ልማት መምሪያ ሕጋዊ እውቅና የተሰጠው አካል ነው። በዚህ ሕጋዊ እውቅና መሠረት ጽ/ቤቱ በቤት አሰጣጥ ላይ የሚደረጉ መድሎዎችን ተከታትሎ በድርጊቶቹ ላይ በፌደራል ሕግ መሠረት ክስ ይመሰርታል።

የአሜሪካ የቤቶችና የከተማ ልማት መምሪያ ይህ በራሪ ወረቀት እንዲዘጋጅና እንዲታተም የገንዘብ አስተዋጽኦ አድርጓል።

# ይህ የእርስዎ መብት ነው



# እኩል ቤት የማግኘት መብት!


**የሰብአዊ መብቶች ዲ.ሲ. ጽ/ቤት**
441 4th Street N.W., Suite 570N
*ወይም*
3220 Pennsylvania Avenue S.E.
Washington, D.C.
(202) 727-4559

# በአካባቢ እና በፌዴራል ሕግ የተከለከሉ ጉዳዮች

**በቤት ሽያጭና ክራይ ሂደት ውስጥ የሚከተሉት ጉዳዮች በሕግ የተከለከሉ ናቸው።**

- ቤት ለማከራየት ወይም ለመሸጥ ፍቃደኛ አለመሆን፣
- ለመደራደር አሻፈረኝነት
- ለተወሰኑ የህብረተሠቡ ክፍሎች የቤት አገልግሎት ለመስጠት እምቢተኛ መሆን፣
- ግለሰቦች በቤት ውስጥ እንዳይኖሩ መከልከል፣
- የተለዩ ግዴታዎችን እና ሁኔታዎችን ወይም ጥቅሞችን መፍጠር፣
- የተለዩ የቤት አገልግሎቶችን ወይም ቁሳቁሶችን ማቅረብ፣
- ቤቱ ለሽያጭ ወይም ለኪራይ ይፈለጋል በማለት የተሳሳተ መረጃ መስጠት
- የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት አከራዮች ቤታቸውን እንዲሸጡ ወይም እንዲያከራዩ ማግባባት፣
- ግለሠብን ከሚመቸው የመኖሪያ ሥፍራ ማፈናቀል እና ግለሠቡን የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርግ መጮትጮት
- የቤት ሽያጭን ወይም ኪራይን በተመለከተ አንድ ዜጋ አገልግሎት ወይም በተቋማት ውስጥ አባልነት እንዳያገኝ ሆን ብሎ መከልከል።

**ከዚህ በተጨማሪም የሚከተሉት ኢ-ሕጋዊ የሆኑ ድርጊቶች ናቸው።**

- እኩል የቤት አገልግሎት መብታቸውን በአግባቡ የማይጠቀሙ ዜጐችን ማስፈራራት፣ ማስገደድ፣ በመብታቸው ውስጥ ጣልቃ መግባት ወይም አላግባብ የሆነ እርዳታ ማበርከት፣
- የዘር፣ የቀለም፣ የብሔር፣ የሐይማኖት፣ የፆታ፣ የቤተሠብ ደረጃ ወይም የአካል ጉዳተኝነት መድልኦ የማያንፀባርቅ ማስታወቂያ ወይም መግለጫ ማውጣት፣
- አቤቱታ በሚያቀርቡ ወይም ለአቤቱታው ምሥክር የሚሆኑ ዜጐች ላይ የበቀል እርምጃ መውሰድ።

እኩል ቤት የማግኘት መብት (42 ዩ.ኤስ.ሲ. 3601፣ እ.ኤ.አ. በ1968 የታወጀው የሲቪል መብቶች ሕግ አንቀጽ 8 እንዲሁም እ.ኤ.አ. በ1988 የተሻሻለው የቤቶች አስተዳደር ሕግ) ዘርን፣ ቀለምን፣ ብሔርን፣ ሐይማኖትን፣ ፆታን፣ አካለስንኩልነትን፣ የቤተሠብ ደረጃን (ማለትም ከ18 ዓመት በታች የሆኑና ከወላጆቻቸው ወይም ከሕጋዊ ሞግዚቶቻቸው ጋር የሚኖሩ ልጆችን፣ እርጉዝ ሴቶችን እንዲሁም ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆችን የሚያስተዳድሩ ዜጐችን ጨምሮ) በመመርኮዝ በቤቶች ሽያጭ፣ ኪራይ ወይም ግንባታ ወቅት የሚደረጉ መድሎዎችን ይከለክላል።

እ.ኤ.አ. በ1977 የተሻሻለው የዲ.ሲ. ሰብአዊ መብቶች ሕግ የፌደራል የቤቶች አስተዳደር ሕግን ይተካል። በተጨማሪም ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ጉዳዮች የሕግ ከለላ ይሰጣል።

- ዕድሜ
- የጋብቻ/የቤተሠብ ሁኔታ
- ተክለ ሰውነት
- የመኖሪያ/የንግድ ቦታ
- የፍትወተ ዝንባሌ
- የቤተሠብ ኃላፊነት
- የፖለቲካ አቋም
- የትምህርት ደረጃ
- የገቢ ምንጭ
- ጾታን ማንጸባረቅ ወይም አገላለጽ

**ከዚህ ሕግ የማይካተት የቤት ዓይነት:**

ሕጉ በመንፈሳዊ ድርጅቶች በሚንቀሳቀሱ የንግድ ባልሆኑ ቤቶች እንዲሁም ለአባላቶች መኖሪያነት ብቻ በሚያገለግሉ የግል ክለቦች ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

# የቤት አገለግሎት መድልዎ ደርሰቦታል?

ከሌላ ሀገር በመምጣት ወይም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለመናገር የመኖሪያ ቤት ተከልክለዋል?

አከራዩ በዘር፣ በቀለም ወይም በብሔር ላይ በመመርኮዝ የከፈሉን የተከራዮች ቤቶች አድሶ የገሚሶቹን ሳያድስ ቀርቷል?

ሰፊ ቤተሰብ ስላሎት አከራዩ ተጨማሪ የኪራይ ክፍያ ጠይቆታል? ወይም ቤቱን አላከራይም ብሎታል?

በዊልቸር ስለሚሄዱ አከራዩ ቤቱን እንዳይከራዩ ከልክሎታል?

በክፍል 8 የክፍያ ደረሰኝ የተነሳ አከራዩ ቤት አላከራይም ብሎታል?

**ከላይ የተዘረዘሩት በደሎች ከተፈፀመበት ጉዳዩን በሚከተለው አድራሻ**

**ለዲ.ሲ የሰብአዊ መብቶች ጽ/ቤት ያስታውቁ።**
ስልክ (202) 727-4559